Elder SAFE

Charles E. Smith Life Communities

*አረጋውያንን ከጉዳት መጠበቅ*

**የአረጋውያን ደህንነት** ማዕከል ለአረጋውያን ጉዳት ጠንካራ እና አስተማማኝ ምላሽ ለመስጠት ከአካባቢው ኤጀንሲዎች፣ ሆስፒታሎች፣ እና የማህበረሰብ አገልግሎት ድርጅቶች ከመሰሉ የህብረተሰባችን አጋሮች ጋር ይሰራል።

## የአረጋውያን ጉዳት ምንድን ነው?

**የአረጋውያን ጉዳት በሚከተሉት አንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ** መንገዶች አረጋውያን ላይ የሚደርስ እንግልት ነው።:

- አካላዊ: ሃይል መጠቀም (እንደ መምታት ወይም መግፋት) ህመም፣ ጉዳት ወይም የአካል ጉዳት ማድረስ፣ የአካል እቀባዎችን ወይም መድሀኒቶችን ያለ አግባብ መጠቀም
- ወሲባዊ: ማንኛውም ያለ ፍቃድ የሚደረግ ወሲባዊ ንክኪ
- ስነ ልቦናዊ: የስሜታዊ ወይም የአእምሮ ጤናን የሚያውኩ በደሎች፤ ማስፈራራት፣ ድንፋታዎች፣ ትንኮሳ፣ ማዋረድ፣ ማቃለል፣ ወይም ማግለልን ጨምሮ
- ንቀታዊ: መሰረታዊ ፍላጎቶችን ሆን ብሎ መከልከል፤ ምግብን፣ ልብስን፣ መጠለያን፣ መድሃኒትን፣ ወይም የግል ንጽህናን ጨምሮ
- የገንዘብ ነክ ብዝበዛ: የአረጋዊያንን ገንዘብ፣ ንብረት፣ ወይም ሀብት አላግባብ መጠቀም

## አረጋውያን ደህንነት እንዴት ሊረዳ ይችላል?

**እድሜያቸው የገፉትን አረጋውያንን ለመንከባከብ ያለን ቁርጠኝነት** ከካምፓሳችንም አልፎ የሄደ ነው። የቻርልስ ኢ. ስሚዝ ማህበረሰቦች በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ በአይነቱ ልዩ የሆነ የመጀመሪያ ፕሮግራም የሆነውን የአረጋውያን ደህንነት ማዕከል ያቋቋመው:

- በኤምዲ፣ ዲሲ እና ሰሜን ቪኤ ካሉ የማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ሪፈራል መቀበል
- ምስጢሩ የተጠበቀ ምክር፣ ህክምና፣ እና የፈውስ አገልግሎቶችን የሚጨምር ደህንነቱ የተጠበቀ ጊዜያዊ መጠለያ ማቅረብ
- እድሜያቸው ለገፉ አረጋውያን መብት መከራከር
- አስተማሪ ፕሮግራሞችን በማቅረብ ለማህበረሰብ፣ አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ተንከባካቢዎች፣ እና የእምነት መሪዎች ስለ አረጋውያን ጉዳት እውቀት ማዳበር

## የአረጋውያን ጉዳት ማስጠንቀቂያ ምልክቶች

እድሜው የገፋው አረጋዊ ይህንን ነውን...?

- ተንከባካቢውን የሚፈራ
- ከተንከባካቢው አስፈላጊውን ድጋፍ የማይቀበል
- ከቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ ወይም ሌሎች ባለሙያዎች ጋር በግል ለመጨዋወት የተከለከለ
- የሚያለቅስ፣ የተማረረ፣ የተንዘፈዘፈ፣ ግራ የተጋባ፣ ወይም መንፈሱ የተረበሸ
- የተገለለ፣ የተጨነቀ፣ ስሜት አልባ
- ከሰዎች ጋር ወይም በአካል የተገለለ
- እራስን የሚጎዳ ጸባዮችን ምልክት የሚያሳይ
- እንደ ቆሻሻ ልብስ፣ የገላ ጠረን የመሳሰለ የግል ንጽህና ያጓደለ
- መሰረታዊ ፍላጎቶች ያጣ፣ ወይም ቤቱ ውጥንቅጡ የወጣ
- ምክን ያቱ ባልታወቁ ሰምበሮች፣ ቃጠሎዎች፣ መቆረጥ፣ ወይም የቀበቶ ምልክቶች የሚሰቃይ
- ያለፍቃድ ከወጣ ገንዘብ ወይም የክሬዲት ካርድ መጠቀም ያጋጠመው

## ለማን ይደወል?

ይህንን ካርድ ለመጠቀም ይያዙ። የአረጋውያን ጉዳት የሚጠረጠር ከሆነ፣ **911** ይደውሉ ወይም በማህበረሰብዎ ያለውን የአዋቂ ጥበቃ አገልግሎቶች (ኤፒኤስ) ቢሮን ያግኙ።

- በሞንትጎመሪ ካውንት፣ ኤምዲ, **240.777.3000**
- በሌሎች የሜሪላንድ ካውንቲዎች, **1.800.917.7383**
- በዋሽንግተን ዲሲ, **202.541.3950**
- በቨርጂኒያ, **1.888.832.3858**

Elder SAFE
Charles E. Smith Life Communities

አረጋውያን ደህንነት ነጻ የስልክ መስመር: **301.816.5099**
www.eldersafe.org | www.smithlifecommunities.org

**የአረጋውያን ደህንነት™ ማዕከል** የቻርልስ ኢ. ስሚዝ ማህበረሰቦች ፕሮግራም ነው